# ትክክለኛ አማራጭ!

ብርሃኑ (ከአዲስ አበባ)

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ አንድ ሆኖ የሚቆመባቸው መሰረታዊ ሁኔታዎች ሁለት ይመስሉኛል። አንደኛው የአገሩ ልዑላዊነት ሲደፈር በጋራ ተነስቶ ጠላቶቹን በመፋለም ድል የነሳባቸው የታሪክ ምዕራፎች ናቸው።ይህም አገራችን ለዘመናት በውጭ ወራሪ ኃይሎች ሳትንበረከክ በክብር እንድትጠበቅ አስችሏል።

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ከጫንቃቸው አልወርድ ብሎ ሲያዋርዳቸው የኖረ ድህነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ድባቅ ለመምታት ከጫፍ ጫፍ በአንድ መንፈስ በመረባረብ ላይ ናቸው። ለዚሁ አንድነታቸው ከሚያጠናክሩ የልማት አጀንዳዎች መካከል ዜጎች በአገራቸው እንዲኮሩ፣ ሲያፍራቸውና አንገታቸውን ሲያስደፋ የኖረውን የድህነት ታሪክ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀየር ያስችላል ተብሎ የታቀደው ፕሮጀክት ይፋ ሆኗል። ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም የሚጠይቀውን ከፍተኛ በጀት ካለ የዜጎች ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ እንደማይሳካ ተገቢውን ግንዛቤ በመያዛቸው የፊናቸው እንዲወጡ ቆርጠው ተነስተዋል። እንዲያውም ሙግታቸው እየሆነ ያለው ‘’ አሁን ይህቺ ምን ትበቃለች?’’ የሚለው ነበር።

በመጋቢት ወር መጨረሻ ይፋ የተደረገው ፕሮጀክት የዘመናት ሕልሙን እውን ሊያደርግ ለዘመናት ሲያንገበግበው የቆየውን ጉዳይ ሊመልስለት የሚያስችል በመሆኑ ምላሹ ፈጣን መሆኑ አያስገርምም።

ለትውልዶች ውሃውን ብቻ ሳይሆን፣ ለም አፈሩን ጭምር ለባዕዳን እየገበረ አሳልፎ የሚሰጠው ታላቁ ወንዛችን ከበይ ተመልካችነት ወጥተን የልማት ጥያቄውን ለመመመለስ የሚያስችል ሆኖ በማግኘቱ አንጀቱን አርሶታል። የታላቁ የሚሌኒየም የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የአገሪቱን ሕዝቦች አንድነታቸው ደጋግመው እንዲያሳድሱ አድርጓቸዋል።

ኢትዮጵያ ከገዛ አገሯ መንጭቶ ያለ ጥቅም ወደ ውጭ ሲፈስ የኖረው ወንዝ ተገድቦ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረጓ ለዘመናት ሕልውናዋን ሲፈታተኑት የነበሩትን የግብፅ መሪዎች እንደሚፈጥሩት ውዥንብር ሳይሆን፣ የአባይ ተፋሰስ አባል አገሮች በተፈጥሮ ሀብቱ ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ለመጠቀም እንደሚችሉና ሀገራችንም በጋራ ልማት እንደምታምን በተደጋጋሚ አቋምዋን እየገለፀች መጥታለች።

የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ በተለይ ከግብፅ ጋር ያለውን ግንኙነት የአባይ ወንዝ 85 በመቶ መነሻ የሆነችው አገራችን በጥንቃቄ እንደምትመለከተው ያስረዳል። ሁለቱን አገሮች በጥብቅ ያቆራኛቸው የተፈጥሮ ሀብት ግብፅና የአባይ ጉዳይ በአግባቡ መያዝ እንዳለበትም ያሳስባል።

ኢትዮጵያ ወንዙን ለመስኖ ልማት እንዳትጠቀምበት ሲረባረቡ፣ ከሱዳን ጋር በመሆንም የአባይ መፍለቂያዋ አገር አንድ ሊትር ውሃ እንዳታገኝ ለማድረግ የተስማሙበት ታሪካዊ ሁኔታ ነበር። በተለይ ግብጻውያን ‘’ ኢትዮጵያ አባይን ከተጠቀመች ግብፅ ትጎዳለች’’ የሚል የተዛባ አስተሳሰብ ይዘው ቆይተዋል።

ጭልጥ ባለ ምድረ በረሃ ላይ የተገነባው የአስዋን ግድብ በየዓመቱ 10 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በትነት እንዲጠፋ የሚያደርግና ይህም ወደ ተከዜ ወንዝ በዓመት ከሚገባው የውሃ መጠን የበለጠ መሆኑን የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ያስረዳል።

ግብፅ ያላትን አባካኝ ውሃ አጠቃቀም ለመቀነስ ሳትችል መቅረቷ ሳያንሳት፣ የአባይን ውሃ ዘላቂና ፍትሃዊ በሆነ ክፍፍል ለመጠቀም እስከ አሁን ፈቃደኛ አይደለችም። ምንም እንኳን ከዜጎቿ መካከል የተወሰኑት ከዚህ የንፉግነት አስተሳሰብ እየተሳቡና ጉዳዩን እየተረዱት ቢመጡም።

የኢትዮጵያ አኩራፊ ኃይሎችንና ጸረ ሰላም ኃይሎችን በየጊዜው እያስታጠቀች ከአሸባሪው የኤርትራ መንግሥት ጋር እንደምትተበበርም ይታወቃል። አሁን ግን አባይ ብቻ ሳይሆን፣ ግብፅ ለጋራ ተጠቃሚነት ልብ የምትገዛበት ወቅት የግድ ሆኗል።

ኢትዮጵያ ፈጣን ልማቷን ለማረጋገጥ የተያያዘችውን እንቅስቃሴ ለማሳካት የተፈጥሮ ሀብቷን በአግባቡ መጠቀም የግድ ይላታል።ለዚህም በተፈጥሮ የታደለችውን የውሃ ሀብት ተጠቅማ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጨት መቻል አለባት። ኤሌክትሪክ የኃይል ምንጭ በመሆኑ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ወሳኝነት አለውና ይህንን ሀብት ተጠቅማ የራሷን ፍላጎት በማሟላት ለጎረቤት አገሮች በመሸጥ ጭምር ከልማቱ የበለጠ ተጠቃሚ መሆን ትችላለች። የአባይ እናት የአቅምና የፖሊሲ ማነቆዎች አላላውስ ብለው ለዘመናት ሲያንከራትቷ በመቆየታቸው ነው እንጂ፤ ወንዙን ለዚህ ጥቅም ማዋል የነበረባት ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከሺህ ዓመታት በፊትም ቢሆን መሆን የነበረበት ትክክለኛ አማራጭ ነበር። ሕዝቦቿን ሲያቃጥላቸው የነበረውም ይኸው ነውና።

ፕሮጀክቱ በአፍሪካ ቀንድ አገሮች መካከል ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠርም ጠቀሜታው አያጠያይቅም።በሰላምና በድርድር መንፈስ የተፈጥሮ ሀብቱን በጋራ እየተጠቀሙ ልማቱን ማካሄድ የሚያስገኘው ጥቅም አንድና ሁለት የለውም።

የጋራ መተማመን መንፈስን በማጎልበት የትኛውም ወገን ተጎጂ የማይሆንበትን ፍትሐዊ አሰራር በማስፈን ከልማቱ ተጠቃሚ መሆን ያለበለዚያ  ኢትዮጵያ እየተጎዳች እኛ ብቻ እንጠቀም ማለት ኢ-ፍትሃዊነት ነው።

ፖሊሲው በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ጊዜና ፍትህ የኢትዮጵያ የልማት አጀንዳ መሆናቸው እንደማይቀር ይገልጻል። አዎን ጊዜው ደረሰና ከአባይ ወንዝ 5ሺህ 250 ሜጋ ዋት ሃይል ልናመነጭ በመረባረብ ላይ ነን።

ጥቁርና ነጭ አባይ በአንድነት "ናይል" የሚባል መጠሪያ አላቸው።በናይል ስም የተሰባሰቡት 10 አገሮች የሚያስተባብር ድርጅት ተቋቁሞ ይህንን የተፈጥሮ ሀብት ለጋራ ጥቅም እንዲያውሉት የሚያስችል የስምምነት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል።

ምናልባትም ግብጻውያን እስካሁን ‘’አሻፈረኝ’’ ያሉት እንዲሁም በዚሁ ኢ-ፍትሐዊ አቋማቸው ጸንተው እስከ ግንቦት 5 ቀን 2003 (ሜይ 13 ቀን 2011) ድረስ ሳይፈርሙት ቀርተው ወደ አፍሪካ ኅብረት መዝገብ ቤት ለጊዜውም ቢሆን ሊገባ የሚችለውን ስምምነት ለማየት ችዬ ነበር።

‘’ ሰነዱ ምን እጥረት ቢኖረው ነው ግብፅና ሱዳን ሳይፈርሙት የቀሩት?’’ የሚለው ጥያቄ ቀድሞም ይመላለስብኝ ስለነበር በ 40 ገጾች ተሰድሮ 45 አንቀጾችና አባሪዎች ያሉትን ሰነድ ተመለከትኩት። በእኔ አመለካከት ለአንድ ዓመት ለፊርማ ክፍት የሆነውን ሰነድ ላለመፈረም ዋነኛ ሰበቡ ስግብግነት ወይም ራስን ወዳድነት ሆኖ ይሰማኛል።

የስምምነቱ ሰነድ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሚያወራው ነገር አንድ ጉዳይ ብቻ ነው። የናይል ተፋሰስ አገሮች የተፈጥሮ ሀብቱን በጋራ በማልማት እንጠቀምበት ይላል። ሀብቱ የአገሮቹን ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ተጠብቆ እንገልገልበት ዋነኛ መልዕክቱ ሆኖ ሰፍሯል።

በዚህም የአገሮቹ ሕዝቦች በጋራ የሚያስተሳስራቸውን የተፈጥሮ ሀብት ለዘላቂ ልማት ሊጠብቁት፤ አካባቢያቸውን ሊንከባከቡትና በተቀናጀ አስተዳደር ለአሁኑም ሆነ ለመጪዎቹ ትውልዶች ጥቅም ላይ ሊያውሉት የሚችል አቅምና ጉልበት እንዲኖራቸውም በአንድነት ተሳስበን እንጠቀምበት ይላል። የስምምነቱን መግቢያም የሚያትተው ይህንኑ ነው።

የስምምነቱ አንቀጽ አንድም የተፋሰሱ አጠቃቀም፣ ልማት፣ጥበቃ አያያዝና አስተዳደር በጋራ ተቋማዊ ትብብር ይሆናል ይላል።

በአንቀጽ ሦስት ሥር የተቀመጡት አጠቃላይ መርሆዎች ደግሞ ትብብርና ዘላቂ ልማትን በእኩልነትና በፍትሐዊነት መገልገልን ዋነኛ ነጥቦች አድርጎ ያስቀምጣቸዋል።

የተፋሰሱ አባል አገሮች ውሃውን በግዛታቸው ክልል ውስጥ የመጠቀም መብት ፈጽሞ ለድርድር የማይቀርብ መብት መሆኑንና ከሌሎች መሠረታዊ መርሆዎች ጋር እንደማይጋጭም አስረግጦ ያስረዳል።

አገሮቹ በተፋሰሱና በሥነ ምህዳሩ ጥበቃና አያያዝ የተናጠልና የጋራ ድርሻ እንዳላቸው የኅብረተሰቡን ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም ይገልጻል። በተፋሰሱ አጠቃቀም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በሰላማዊ መንገዶች መፍታት እንደሚያስፈልግ በዚህ አንቀጽ የተቀመጠ ሌላው ነጥብ ነው።

የውሃ ሀብት ለሕይወት፣ ለልማትና ለአካባቢ ባለው ጠቀሜታ ላይ ተመስርቶ ማስተዳደር እንደሚያሻና ይህንንም በጋራ መገልገል እንደሚያስፈልግ የስምምነት ማዕቀፉ በአፅንኦት ያስገነዝባል።

ውሃ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድርሻ በመረዳት አጠቃቀሙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን በማስቀደም መሆን እንደሚገባውና ይህ ሲሆንም መሠረታዊውን የሰዎች ፍላጎት መጉዳትና የአካባቢው ሥነ ምህዳርን ማዛባት እንደሌለበት ያመለክታል። የውሃ ደህንነት በተፋሰሱ አገሮች በሙሉ መረጋገጥ እንደሚገባውም ያስገነዝባል።

አንቀጽ አራት ወንዙ በፍትሃዊነትና በተመጣጣኝ መንገዶች ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚገባ ይተነትናል። ተከታዩ አንቀጽ በተፋሰሱ ላይ ጉዳት ሳያደርስ መጠቀም አስፈላጊነቱን ይገልጻል። ከዚህም በኋላ ያሉት አንቀጾችም ቢሆኑ በስምምነቱ የተቀመጡትን መሠረታዊ መርሆዎችን እያብራሩ ይቀጥላሉ እንጂ ወንዙን ለአንዱ ወይም ለሌላው አገር በግል ይዞታ (በሞኖፖል) እንዲገለገል የሚፈቅድ ሐሳብ አያንጸባርቁም።

በአጠቃላይ ስምምነቱ ሲታይ ተፈጥሮ ያደለችንን ሀብት በጋራ በመጠቀም ልማትና ዕድገት ለማምጣት እንጠቀምበት በሚል አንድምታ አለው። ለዚህም ነው ስድስት አባል አገሮች እስካሁን ስምምቱን በመፈረም የሌሎችን መፈረም በመጠባበቅ ላይ የሚገኙት። በመጨረሻም ስምምነቱ የወል መተዳደሪያ ይሆናል።

የእነ ግብፅ ይህን የጋራ ዕድገት ምንጭ የሆነ ሰነድ አለመቀበል ራስን ያለ ቅጥ በመውደድ ሌሎች አገሮች ከድህነት አረንቋ እንዳይወጡ የድህነት ዕድሜአቸውን ከማራዘም ውጭ ምን ሊባል ይችል ይሆን?

ኢትዮጵያ በአገሪቱ ያሉትን ተፋሰሶች የምታስተዳድርበት ዓዋጅ ሐምሌ 16 ቀን 1999 አውጥታለች። ዓዋጁ የውሃ ሀብቱን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችላት ነው።

ዓዋጁ ‘’ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር በተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ አግባብ ያላቸው አካላት ውሳኔዎቻቸውና ዕቅዶቻቸውና በውሃው ዑደትና በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ የሚያስከትሏቸው ውጤቶች ላይ የአመለካከት የፍላጎና የግንዛቤ ልዩነት ቢኖራቸውም ተባብረው እንዲሰሩ የሚጠይቅ በመሆኑ’’ በማለትም በመግቢያው ላይ አስፈላጊነቱን ይገልጻል።

የአገሪቱን 12 ተፋሰሶች የሚዘረዝረው ይህ ዓዋጅ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስቀምጠው ተፋሰስ አባይን ነው። አባይ በኢትዮጵያውያን ልቡና ያለውን ድርሻና ካለው ዓለም አቀፍ ባህርይ አኳያ ተመዝኖ የመጀመሪያ ደረጃ ቢሰጠው አይበዛበትም።

ዓዋጁ ’’ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር’’ ማለት ውሃ እንደ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሀብትነቱ በተፋሰስ ውስጥ ካሉ የተለያዩ አጠቃቀሞች ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ ሆኖ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው የውሃ ሀብት ልማት እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ያመለክታል።

‘’ የውሃ ሀብት’’ ማለት መጠንና ጥራትን ባካተተ ሁኔታ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሲሆን የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርንና ረግረጋማ መሬትን ያጠቃልላል’’ በማለት ይተነትናል።

እንዲሁም ‘’ የተፋሰስ ዕቅድ’’ ማለት በውሃ አጠቃቀም ፍትሃዊነትንና ቀጣይነትን በማረጋገጥ ዓላማ ላይ የተመሠረተና የረዥም ጊዜ ራዕይ ያለው ስትራቴጂክ የተፋሰስ የውሃ ሀብት ዕቅድ ነው’’ ሲልም ያብራራል።

በዓዋጁ መሠረት የተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶች ይቋቋማሉ። ምክር ቤቶቹ ፍትሃዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ ለሕዝብ ሕይወት መሻሻል የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናሉ። ለዚህም የማበረታታትና የመቆጣጠር ሥራዎችን በሥልጣን ክልላቸው ውስጥ እንደሚያከናውኑም ይገልጻል።

የወሰን ተሻጋሪ ተፋሰሶች አጠቃቀምን በሚመለከት የሚያከናውኗቸው ተግባራት በውሃ አጠቃቀም ረገድ ለሚነሱ አለመግባባቶችን መፍትሄ የመስጠትና ከጎረቤት አገሮች ጋር ማወያየት ላለበት አካል መረጃና የምክር ድጋፍ እንደሚገልጽ የሚያብራሩ አንቀጾችም አሉት።

ዓዋጁን ለማስፈጸም የሚያስችል በርካታ ሥልጣንና ተግባራትም ይኖሩታል። በተጨማሪም የተፋሰስ መረጃ ሥርዓትን በመዘርጋት ሥራውን ያከናውናል። ለዚህም ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል። አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጣልቃ ገብ ሥራዎችን ወይም ፕሮጀክቶችንም ለይቶ ያወጣል።

እንዲሁም የተፋሰስ ዕቅድን በማዘጋጀት ሥራ ላይ የሚያውልበት ሁኔታም ተፈጥሮለታል። ይህ ሁሉ እንግዲህ በአገር ደረጃ በግዙፍነቱና ለዘመናት ሳንጠቀምበት የኖረውን የውሃ ሃብታችንን ይመለከታል።

መንግሥት በአገሪቱ የግዛት ክልል ውስጥ የሚገኙትን ተፋሰሶች ለጥቅም ለማዋል ይህን የመሰለ ታላቅ ተግባር የሚያከናውን ተቋምም ለመመስረት ጥረት እያደረገ መሆኑን ያሳያል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ አባይን ይዘን በድርቅና በረሃብ ከመጠቃት የአባይ አባት ሆነን በውሃ ጥም ከመቸገር የምንወጣበት ታላቅ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ የተዘረጋው ፕሮጀክት በወንዙ ባለቤታችን የአንድ ከፍተኛና ታሪካዊ ሥራ ሊከናወንበት መሆኑን መስማት በራሱ ያስደስታል።

ለዚህ ከፍተኛ ወጪ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት በማጣት እንደምንቸገር ወትሮም ይታወቃል። አማራጩ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የፕሮጀክቱን የመሠረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ የተናገሩት ነው። አባይን ለጥቅም በማዋል መጠቀም የምንችልበትን አማራጭ እንድናይ የሚያስገድድ ነው።

ሕዝቡማ ምርጫችንማ ብሎ የሚጠበቅበትን ማድረግ ጀምሯል። ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም በአንድ ልብ መነሳቱ በአጭር ጊዜ የሰጠው ምላሽ ይገልጻል። ዛሬ በአገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን፤ በባህር ማዶ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለፕሮጀክቱ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ መረባረብ ይዟል። ሚሊዮኖች ስለማይበቁ ቢሊዮኖችን ለመለገስ ጊዜው ይረዝም እንደሆን እንጂ፤ መሳካቱ እንደማይቀር ከጅምሩ በመነሳት መደምደም ይቻላል።

ለፕሮጀክቱ ማከናወኛ የሚሆን ገቢ ለማሰባሰብ መንግሥት የቦንድ ሽያጭ መጀመሩ እንደ ፕሮጀክቱ ሁሉ ታላቁ መላ ነው። ዜጎች በተናጠልና በቡድን እየሆኑ ቦንዱን መግዛት ጀምረዋል። ወለድ ያለውና የሌለው መሆኑ ገቢው እንደ እምነቱና ፍላጎቱ ለመጠቀም ያስችለዋል።

ኢትዮጵያዊው በሙሉ ልብ የልማት ጉዞውን ከዳር ለማድረስ ደፋ ቀና እያለ ይገኛል። አሁን ያለው ጉዳይ ‘’ ይህቺ ለአባይ ምኑ ነች?’’ የሚለው ከራስ አቅም ጋር የሚደረገው ትግል ነው። ‘’ ያለውን የወረወረ--------‘’ እንደሚባለው በመሆኑ ያለውን በመለገሱ ቀጥሎበታል። በሚቀጥሉት ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት እየሰፋና እየተጠናከረ እንደሚሄድም ጅምሩ ያሳያል። አባይን ለአገር ልማት ሳይገብር ምን ፋታ ይኖረንና!!

በገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራት ያለውን ገንዘቡን ወደ ልማቱ ለማዞር የተጀመረው እንቅስቃሴም ይበል የሚያሰኝ ነው። ዕድሮችም ወደዚሁ አቅጣጫ ለመግባት የሚችሉበት ጊዜ ሩቅ አይመስለኝም።

ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የተዘጋጁ ዜጎችም እየተበራከቱ እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ። ዜጎች በአንድ ልብና ስሜት የተነሳሱበት ጉዳይ በመሆኑ ቁርጠኛ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የተዘጋጁ ሙያተኞች እየጎረፉ ነው።

የቁርስ በጀታቸውን ለሥራው የሚውል ገቢ ለማስገኘት የሚተዉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ብዛትም የሚያስደስት ነው።

መንግሥት፣ የልማትና የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም የሃይማኖት ተቋሞች ከባድ ነገር ግን ሊወጡት የሚችሉ የቤት ሥራ ከፊታቸው እየጠበቃቸው ነው። ኅብረተሰቡን በተለያዩ መንገዶች በማሳተፍ ገቢ በማሰባሰብ ለታላቁ የሚሌኒየም ግድብ ፕሮጀክት ማዋል የመጀመሪያው ተግባራቸው ሊሆን ይገባል።

መንግሥት በዚህ ረገድ የጀመረውን ሥራ በማጠናከር ገቢ የማሰባሰብ ተግባሩን ይበልጥ አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ቴሌ ቶኖችን በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሚዘጋጁበት መንገዶች ይፈጠሩ፤ ከሕጻን እስከ አዋቂዎች ለአባይ ልማት የሚውል ገቢ ለማስገኘት ዘዴዎችን መቀየስ ይችላሉ። ከካናቴራ እስከ  ከረሜላ ያሉ ቁሳቁስ በመሸጥ ገቢ ማግኘት ይችላል። የአባይ ግድብ የቦንድ ዕቁብም ሌላው አማራጭ ሊሆን ይችላል። የታላላቆቹ መሪዎቻችንና የአባይን  ምስሎች የያዙ ፎቶግራፎችን አትሞ በመሸጥም ጠቀም ያለ ገንዘብ ማግኘት ይቻላል።

አባይን ይዘን ችግርን፣ አባይን ሊገድቡብን ይችላሉ በሚል የባዕዳን ተዘዋዋሪ ወረራና ተጽዕኖ ዛሬም አላበራልንም። ችግሮቹን ተቋቁመን ወደ አንድ እመርታ ላይ ደርሰናል። እጅግ ቆራጥነት ባለውና በበሳል አመራር ተነስተናልና የተጀመረውን የልማት ጉዞ ዳር ለማድረስ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ ጥርጥር የለውም።

ህዝቡም ለትውልዶች አንጀታችንን ሲያቃጥል የኖረውን የአባይን ጉዳይ በልማቱ ለማካካስ ከመቸውም በላይ ቆርጦ ተነስቷል። አባይን ለማልማት የሚቆጠብ ገንዘብና ዕውቀት የለም በሚል ጠንካራ መንፈስ እንደሚያሳካው ጅምሩ በራሱ ይናገራል።

**አባይን ለታቀደው ልማት በማዋል ታላቅነታችንን እናስመሰክራለን!!**